**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**
**Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)**

# <u>ድርጅታዊ መግለጫ</u>

ጥቅምት 21 ቀን 2000 (October 29, 2007)

ድርጅታችን ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ከ1964 ዓ/ም አንስቶ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ሉዓላዊነት፤ ለአገር አንድነትና ክብር፤ ለሕዝቧ ነጻነትና እኩልነት፤ ለማሕበራዊ ፍትህ፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለህግ የበላይነት አንዴም ሳያመነታ ለመታገሉ በከፈለው ከፍተኛ መስዋዕትነት አስመስክሯል። በዚህም የትግል ዕድሜው ውስጥ አስከፊ የሆነ የግፍ ጭፍጨፋና የጅምላ ግድያ ሰለባ ሆኗል። ደርግ ከወደቀ በኋላም እርሱን በተካው የህወሃት/ኢሕአዴግ ሥርዓት ተመሳሳይ ግፍ ደርሶበታል፤ እየደረሰበትም ነው።

ይህ ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎ ግን ኢሕአፓ የተነሳበት ዓላማና ያቀዳቸው ሕዝባዊ የፖለቲካ፤ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ፕሮግራሞች እስካሁን በተግባር ዕውን ሊሆኑ አልቻሉም። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ረጅምና መራራ ትግል ከፊታችን ተደቅኖ ይገኛል። ኢሕአፓም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳኑን ሳያጥፍ ውድና ብርቅዬ የሆኑ አባላቱና ደጋፊዎቹ የታገሉለትን፤ የተዋደቁለትንና ከፍተኛውንም መስዋዕትነት የከፈሉበትን ዓላማ ሳይዘነጋ በአገራችንና በሕዝባችን አንድነት፤ ደህንነትና ጥቅም ላይ ሳይደራደርና ግንባሩንም ሳያጥፍ ትግሉን መቀጠል ይጠበቅበታል።

እንግዲህ ባንድ በኩል ለዚህ ለሚጠብቀን መራራ ትግል ስንዘጋጅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውስጣችን የተፈጠሩትና ረዘም ላለ ጊዜ ተመቻችተው የተቀመጡ ሁለት አምባገነናዊ ግለሰቦች ይህን ክቡር ዓላማችንን እንዳናስተገብር ውስብስብ ችግሮች በመፍጠር ዕንቅፋት ሆነውብናል። የሚታገለው ሕዝባችን ተስፋ እንዳይቆርጥና የትግል ሰማዕታቶቻችን የከፈሉት መስዋዕትነትም በከንቱ እንዳይቀር በማሰብ ድርጅታችን በነዚህ ጥቂት አምባገነኖች ተቀይዶ ሲያዝ የከፋና አንድነትን የሚያናጋ ውዝግብ ላለመፍጠር ስንል በትዕግሥት እየተመለከትን ቆይተናል። ችግሩ ከዕለት ዕለት ሊሻሻል ይችል ይሆናል በሚል ተስፋም ስንጓዝ ቆይተናል። አንዳንዴም ድርጅቱ እንዳይጎዳ በማሰብ በከፍተኛ ጥንቃቄ ጉድለቱን ለማረም ሞክረናል። በአባላት ጠቅላላ ጉባዔ የተወሰኑ ድርጅታዊ ፖሊሲዎችና የትግል ስትራቴጂዎች ከሚለዋወጡ አገራዊ፤ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች እየተገናዘቡ በተግባር እንዲተረጎሙ፤ ባገር ቤት ውስጥ ያለው ትግል እንዲጠናከርና ድርጅታችን ለትግሉ የሚጠበቅበትን ድርሻ ማበርከት እንዲችል የምንችለውን ሁሉ ጥረት አድርገናል።

ዴሞክራሲያዊ ኢሕአፓ

*P.O.BOX: 88675, LOS ANGELES, CA 90009 U.S.A*

ሆኖም ግን ይህን ድርጅት እንደግል ንብረቱ ይዞና ተቆጣጥሮ ያቆየው ይኼው ቡድን ደርጅቱን ወደፊት ከሚያራምድ ዓላማ በመነሳት ከአባላት ለሚቀርቡ በጎ ኃሳቦችና ምክሮች ጆሮ የማይሰጥ፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት የማይታይባቸውን የአሠራር ስልቶቹን ለማረም አንዳችም ፍላጎት የሌለው ቡድን መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ አረጋግጦልናል። ከዚህም በተጨማሪ ይኼው ቡድን ወዳጅ ሊሆኑ በሚችሉ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ያካሄዳቸውና የሚያካሂዳቸው አሉታዊ ቅስቀሣዎች፤ እንዲሁም በውስጥ ጉዳያቸው የፖለቲካዊ ጣልቃ-ገብነት እያደረገ በመካከላቸው የበለጠ ክፍፍልና መበጣበጥን ለማምጣት የሚያደርጋቸውን ተንኮሎች ተገንዝበናል።

እነዚህ ድርጅታዊ ችግሮች በሙሉ ፓርቲውን ሊጠቅሙ በሚችሉ መንገዶች እንዲታረሙ ለማድረግ የኢሕአፓ አስቸኳይ ልዩ ጉባዔ ከኦክቶበር 26 –29, 2007 ባለው ጊዜ ውስጥ ተካሂዷል። ነገር ግን ይህ አምባገነናዊ ቡድን አባላቱ በረጋና በሰከነ መንፈስ ተወያይተው ጠቃሚ መፍትኄዎችን ለመሻት እንዳይችሉ በፈጠራቸው በርካታ መሰናክሎች የተነሳ ስምምነት ላይ መድረስ አልተቻለም። ስለዚህም ከፍተኛ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ኢሕአፓን ለማዳን ዴሞክራሲያዊ መተክሎቹን በተቋማት ምሥረታ ለማጠናከር፤ ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማዎችን ለማስተካከል እንዲችል መዋቅሩንና ሕገ-ደንቡን አሻሽሎና አመራር መርጦ በተሳካ ሁኔታ ጉባዔውን ደምድሟል።

ይህ ኢሕአፓን ከአምባገነኖች ቁጥጥር አላቆና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መልኩም በትግሉ የማስቀጠል ውሳኔ ፓርቲውን ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ አባላቱ እስካሁን ላካሄዱት ዕልህ አስጨራሽ ትግል ታላቅ ድል አብሳሪ ዜና ነው። አገራችንን ከጥፋት ለማዳን የትግል ድርሻቸውን ለማበርከት ለሚሹ፤ ነገር ግን ፓርቲው ውስጥ በቆየው ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አሠራር የተነሣ ተመልሰው መቀላቀል ላልቻሉት የቀድሞ አባላቱም ታላቅ የምሥራች ነው። በተለያዩ ምክንያቶችም ዛሬ የዚህ ፓርቲውን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ እንቅሥቀሴ አካል ሳይሆኑ በአምባገነናዊው ቡድን ቁጥርር ስር ለቀሩ የድርጅቱ አባላትም የተሻለ የመታገያ አማራጭ ይሆናል።

ይህ ኢሕአፓን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ መራራ ትግል በድል መጠናቀቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል አቅጣጫ የበለጠ እንዲጠናከርና የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች ሕብረትም በተሻለ መልኩ እንዲቀናጅ የሚያስችል አዲስ በር ይከፍታል። በአገራችን ብሔራዊ ሉዓላዊነት፤ ግዛታዊ አንድነትና በሕዝቧ እኩልነትና ውኅደት ላይ የተመሠረተው አገርን የማዳን ብሔራዊ ትግላችን በሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍ የሚታጀብና የሚጠናከር እንደሚሆን አንጠራጠርም።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

*ዴሞክራሲያዊ ኢሕአፓ*

*P.O.BOX: 88675, LOS ANGELES, CA 90009 U.S.A*